# የኢትዮጵያን ሰፊ መሬት ለሱዳን ለማስረከብ ለመስከረም 29 ቀን 2002 ዓ. ም. (October 9, 2009) ተቀጠረ፤

ከኢትዮጵያ ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ የተሰጠ መግለጫ
መስከረም 16 ቀን 2002 ዓ. ም.
September 26, 2009

ሱዳን ትሪቢውን (Sudan Tribune) የተባለው በእንግሊዘኛ ቋንቋ የሚታተመው የሱዳን ጋዜጣ በመስከረም 8 ቀን 2002 ዓ. ም.(September 18, 2009) ባወጣው እትሙ፡-

"የሱዳን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኢንጂነር ኢብራሂም መሐመድ ሀሚድ September 17, 2009 (በመስከረም 7, 2002 ዓ.ም.) በካርቱም ከተማ ውስጥ በጠሩት ስብሰባ የኢትዮጵያና የሱዳን ጣምራ ኮሚቴ ድንበሩን ሙሉ በሙሉ ለማካለል ዝግጅት ማጠናቀቁን ገልፀው፤ የድንበሩ ማካለል በመስከረም 29, 2002 ዓ. ም.(October 9, 2009) እንደሚከናወን አሳውቀዋል። በዚሁ ስብሰባ የሱዳን ፕሬዚዳንት አማካሪ ሚስተር ሳላህ አብዱላ ጐሽ፣ የሱዳን የመከላከያ ሚኒስትር ጀኔራል አብደል ራሂም መሐመድ ሁሴን፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቋሚ ተጠሪ ሳሚኒ አል-ዋላላ እና ሌሎችም የጣምራ ኮሚቴ አባላት ተገኝተዋል። ስብሰባው አስፈላጊ ዝግጅት መደረጉን ካጠና በኋላ፣ የድንበሩን ክለላ ዳር ለማድረስባ ሊፈጠሩ የሚችሉትን መሰናክሎች ለመቋቋም ይቻል ዘንድ የቅየሳ (Survey) ክፍልን ያካተቱ የሚኒስትሮች ኮሚሽን አቋቁሞ ተለያይቷል" ይላል።

እንግዲህ በሱዳን በኩል ብሔራዊ በሆነና የመንግሥት ተቀዋማትን፣ የዜና አውታሮችን፣ የጦር አባላትንና ሕዝቡን ባስተባበረ መልኩ ዝግጅቱ እየደራ ነው። በእርግጥ ሱዳኖች በታሪካቸው ውስጥ በጭካኔና በኃይል ተጋፍተው ሊያገኙ ያልቻሉትን ሰፊ ውሃ ገብ መሬት አሁን በገፀ በረከት መልኩ ከከሃዲው መለስ ዜናዊና ግብረ አበሮቹ ሲያገኙት ብዙ ፈንጠዝያ ማሳየታቸው የሚጠበቅ ነው።

በአንፃሩ በኢትዮጵያ በኩል የወያኔ መንግሥት ዘርፎች ይሁኑ የዜና አውታሮች የተነፈሱት ነገር የለም። በኢትዮጵያ ውስጥ በኢትዮጵያ ላይ የሚዶለተው ሴራና ክህደት እየተካሄደ የሚገኘው በከፍተኛ ምስጢር ነው።

ወያኔ ለሱዳን ያቀረበው ገፀ-በረከት ከሑመራ እስከ ገሙ ጐፋ ጫፍ ድንበር ያለውን ርዝመቱ 1600 ኪሎ ሜትር የጐን ስፋቱ ከ30እስከ 60 ኪሎ ሜትር የሚደርሰውን ለምና ውሃ-ገብ መሬትና በዚያው የሚገኙትን ደንና ብርቅየ አውሬዎችን ብቻ ሳይሆን በሰሜን ምዕራብ የሚገኙትን ሁለት አንጋፋ ወንዞችን ሽንፋና ጓንግን ጭምር ነው። ይህ የወያኔ ክህደት ግብፅና ሱዳን የአባይን ራስ ለመቆጣጠር የሚያስችላቸውን ታሪካዊ ምኞታቸውንና ሕልማቸውን ባልጠበቁት ወቅትና ስልት ዕውን እያደረገላቸው ነው።

## ውድ ኢትዮጵያዊያን ሆይ!

በአለን አቅምና መንገድ ይህን ሕገ-ወጥ ሥራና የሀገር ክህደት እንድንቃወም ጥሪ እናቀርባለን። ተቃውሞው በሦስት መንገዶች መካሄድ ይቻላል፡-

ሀ) ከኢትዮጵያ ውጭ ላሉ ወገኖቻችን በስልክ፣ በኢ-ሜይል፣ በሬዲዮና በሌሎች በሚቻሉ መንገዶች ክህደቱን ማሳወቅና እነርሱም ይህን የአገር ክህደት በሚመለከት ድርሻቸውን እንዲያበረክቱ ጥሪ ማቅረብ፤

ለ) ለተባበሩት መንግሥታት፣ ለፕሬዚዳንት ኦባማ አስተዳደር፣ ለአውሮፓ ዩንዬን፣ ለአፍሪቃ ኅብረት፣ ለሩስያ፣ ለቻይና፣ ለደቡብ አፍሪቃ፣ ለኡጋንዳ፣ ለኬንያ፣ ለታንዛኒያና ለመሳሰሉት አገሮች በደብዳቤ፣ በኢ-ሜይል የውሉን ሕገ-ወጥነት ማሳወቅ፤ የወያኔን መንግሥት ከሃዲነት ማጋለጥ፤

ሐ) በተለይ ደግሞ በወያኔ አውታሮች ታፍኖና ተከልሎ ለተያዘው በየትኛውም ቦታ ለሚኖረው ኢትዮጵያዊያን ወገኖቻችን በስልክ፣ በደብዳቤ፣ በኢ-ሜይል እና በሌላም በሚቻለው መንገድ ሁሉ የሚከተሉትን ነጥቦች በማንተራስ በስተጀርባቸው የሚሠራባቸውን ክህደትና ሴራ እንዲገነዘቡና ያንን ለመቋቋም ርምጃ እንዲወስዱ ጥሪ ማድረግ፤

1ኛ በድንበር ኮሚቴው አስተባባሪነት 28 የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶችና የሲቪክ ማኅበራት ተሳታፊ የሆኑበት ደብዳቤ ለሱዳን ፕሬዚዳንት ኡመር አልበሽር በJune 02, 2008 ልከዋል። የደብዳቤው ማዕከላዊ ቁም ነገር ፕሬዚዳንቱ የወያኔን የክህደት ኮረቻ በመፈናጠጥ የኢትዮጵያን መሬት ለሱዳን ገቢ ቢያደርጉ ቋሚነት እንደማይኖረውና የኢትዮጵያ ሕዝብም መሬቱን በኃይል ለማስመለስ እንደሚገደድ፤

2ኛ በድንበር ኮሚቴው አስተባባሪነት 25 የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶችና የሲቪክ ማኅበራት ተሳታፊ የሆኑበት ደብዳቤ ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ ለተከበሩ ባን-ኪ-ሙን (Ban Ki-moon) በAugust 21, 2009 ልከዋል። የዚህ ደብዳቤ ዋና ማዕከላዊ ጉዳይም የወያኔና የሱዳን መንግሥት የሚያደርጉት የመሬት መረካከብ ዝግጅት ሕገ-ወጥ እንደሆነና የኢትዮጵያ ሕዝብም ባለቤትነቱን ለማረጋገጥ ምንጊዜም መብቱ የተጠበቀ መሆኑን በመጥቀስ፤

3ኛ አሁን ያለው የወያኔ ጦር የአገሪቱን መሬት አሳልፎ በመስጠት ተግባር ላይ ተሳታፊ ሆኖ መገኘቱ በጣም አሳፋሪ ድርጊት መሆኑን እና የወያኔ የሲቪልና የጦር አስተዳደር አባላት በታሪክም ሆነ በሕግ ተጠያቂ እንደሆኑ፤

4ኛ የመሬቱን መካለል ስምምነትም ሆነ ተግባራዊነት አስመልክቶ አሁን ወያኔ እተዳደርበታለሁ የሚለው ሕገ-መንግሥት እንኳ ሕገ-ወጥ እንደሚያደርገውና የፓርላማ አባላት የሚባሉት ደግሞ ዝምታቸው ከታሪክ ተጠያቂነት እንደማያመልጡ ነው፤

## ውድ ወገኖቻችን ሆይ!

በድንበሩ አካባቢ ያሉ ወገኖቻችን ከቤታቸው፣ ከከብት ግጦሽ ማሠማሪያቸውና ከእርሻ ቦታቸው ተፈናቅለው በከፍተኛ እንግልት ላይ ይገኛሉ። ከነርሱ ውስጥ ጥቂቶቹ የመሬታቸውንና የአገራቸውን ድንበር ለማስከበር ሲሉ እስከ አፍንጫቸው ከታጠቁ ሁለት ጨካኝ መንግሥታት ጋር በመተናነቅ ከፍተኛ መስዋዕትነት በመክፈል ላይ ናቸው። ሁላችንም የነዚህ ወገኖቻችንን እሮሮ ላልሰሙት ወገኖቻቸውና ለዓለም ኅብረተሰብ ማሰማት ኢትዮጵያዊ ግዴታ አለብን።

የኢትዮጵያ ዳር ድንበር በልጆቿ ይከበራል!!

የኢትዮጵያ ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ

Ethiopian Border Afffairs Committee
P. O. Box 9536
Colombus, OH 43209
USA
e-mail: ethiopianborders@gmail.com